# ፖሊስ ምርመራውን ጨረሰ ተጠርጣሪዎችም በዋስ ተለቀቁ

## «ልጃችን ዱላ ቀርቶ ነፋስም አልነካውም»

### *የአቶ አለማየሁ ፋንቱ ቤተሰብ*

በቅርቡ በአውሮፓ ህብረት ኮሚሽን አባላት አማካኝነት በሞያሌ በኩል ከአገር ለመውጣት ሲሞክሩ በፖሊስ ኃይሎች የተያዙት ግለሰቦች ሞያሌ ከተማ በሚገኘው ፍርድ ቤት ቀርበው ጉዳያቸው እየታየ እንደሚገኝ በስፍራው የሚገኙ የኢፍቲን ምንጮች ገለፁ፡፡

ተጠርጣሪዎቹ አዲስ አበባ በሚገኘው የአውሮፓ ህብረት ልዑክ አባላት አማካኝነት ከአገር ለመወጣት ሲሞክሩ መያዛቸው እና ፖሊስ በከፍተኛ ወንጀል እፈልጋቸዋለሁ ያላቸው እነዚህ ተጠርጣሪዎችን በህገ-ወጥ መንገድ ከአገር ለማስኮብለል የሞከሩት ሁለቱ የህብረቱ ሰራተኞች ይህን ድርጊታቸው ተከትሎ መንግሥት ከአገር እንዲባረሩ ማድረጉ ይታወቃል፡፡

የዳያስፖራ ፅንፈኛ ፖለቲከኞች እና አምኒስቲ ኢንተርናሽናል የኢትዮጵያ መንግሥት በተጠርጣሪዎቹ ላይ ድብደባና ስቃይ አድርሷል በማለት ያቀረቡት ዘገባ ከእውነት የራቀ እና ተጠርጣሪዎቹም በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ በፍርድቤቱ ጉዳዩን በመከታተል ላይ የሚገኙት ምንጮቻችን ጠቁመዋል፡፡ የኢትዮጵያ ህገ-መንግሥት በሚፈቅደው መሰረት መብታቸውን በመጠቀም ላይ ይገኛሉም ብለዋል፡፡

ተጠርጣሪዎቹ ከፍርድ ቤት ፈቃድ ውጪ ለፖሊሶች ቃላቸውን ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተው ይህ መብታቸው ተጠብቆላቸው የፍርድ ሂደቱ እንደቀጠለም ጉዳዩን የያዙት አቃቤ ህግ፣ የፖሊስ መርማሪ እንዲሁም ተጠርጣሪዎቹን ጠቅሰው ምንጮቻችን ያደረሱን ዜና አመልክቷል፡፡

በተጨማሪም አምነስቲ ኢንተርናሽናል እና የዳያስፖራ ፖለቲከኞች ተጠርጣሪዎች አካላዊ ድብደባ እና እንግልት ደርሶባቸዋል በማለት ያናፈሱት ወሬ ውሸት መሆኑን

ተጠርጣሪዎቹ ራሳቸው ዳኛው ፊት ቀርበው ማረጋገጣቸውን ምንጮቻችን አክለው አስታውቀዋል፡፡

አንድ ስማቸውን መግለፅ ያልፈለጉ የአውሮፓ ዲፕሎማት እንደገለፁት ደግሞ «የተፈጠረው ነገር የአምነስቲ ኢንተርናሽናልን ኢ-ተአማኒነት ገሃድ ያወጣና ያልተረጋገጠ መረጃን መሰረት በማድረግ እንደ እርግጠኛ ምንጭ ወገናዊና የተዛቡ ወሬዎችን የሚያሰራጩት ወገኖችን ማንነት ያጋለጠ ነው» ሲሉ ገልፀዋል፡፡ ድብደባና ስቃይ ማድረስ በኢትዮጵያ ህገ-መንግሥት ህገ-ወጥ የሆነ ተግባር ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የህግ አስፈፃሚ አካላት ዘንድም የማይፈፀም መሆኑን መታዘባቸውን እኚህ ዲፕሎማት አክለው ገልፀዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በቅርቡ በህገ-ወጥ መንገድ ከአገር ሊወጡ ሲሉ ሞያሌ ድንበር ላይ ተይዘው በቁጥጥር ስር የዋሉትና ፖሊስ በከፍተኛ ወንጀል እፈልጋቸዋለሁ ያላቸው አራት ተጠርጣሪዎች በዋስ መፈታታቸውን የኢፍቲን ምንጮች ገለፁ፡፡

ፖሊስ ምርመራውን አጠናቆ ለፍርድ ቤት ማቅረቡን የገለፁት ምንጮች «ፖሊስ እነዚህ ተጠርጣሪዎች ለጊዜው በዋስ ተለቀው ክሳቸውን እንዲከታተሉ አድርጓል፡፡» ብለዋል፡፡ በዋስ ከተፈቱት ተጠርጣሪዎች መካከል ወ/ሮ የአለምዘውድ በቀለ፣ አቶ አብዱልቃድር አብዲ፣ አቶ አዳነ ሽዋ እና አቶ ፋሲል አሰፋ ናቸው፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ህገ-መንግሥታዊ ስርዓቱን በኃይልና በአመፅ ለመገርሰስ ሞክረዋል በሚል በቁጥጥር ስር በሚገኙት የቀድሞ የቅንጅት አመራሮች አንዲፈቱ፣ የኢኮኖሚ መናጋትና የእርስ በርስ ግጭትን የሚቀሰቅሱ ፅሑፎችን የያዙ የቀን መቁጠሪያ ህገ-ወጥ ህትመትና ስርጭት ጋር በተያያዘ በቁጥጥር ስር ውለው የነበሩት አቶ ዓለማየሁ ፋንቱ እስር ላይ በነበሩበት ወቅት ድብደባና እንግልት ደርሶባቸዋል በማለት አምነስቲ ኢንተርናሽናል ያቀረበው ዘገባ ፍፁም የተሳሳተ እንደሆነና ግለሰቡ በአሁኑ ወቅት ከእስር ተለቀው በአካል ያነጋገሯቸው አንድ ከፍተኛ ዲፕሎማቲክ መግለፃቸው ምንጮቻችን ጨምረው ገልፀዋል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የአቶ አለማየሁ ፋንቱ ቤተሰብ አባል ለሆኑት ስለሁኔታው ባቀረብንላቸው ጥያቄ «ልጃችን ዱላ ቀርቶ ነፋስም አልነካውም በጣም ደህና ነው ምንም የሆነው ነገር የለም በቀን ሁለት ጊዜ እንደልባችን ሄደን እንጠይቀዋለን እናገኘውም ነበር የሚወራው ወሬ የፈጠራና ከኪሳቸው እያወጡ የሚያወሩት ወሬ ነው ከውጭ አገርም ዘመዶቻቸው ደውለው ሲጠይቋቸው ይህንኑ ገልፀውላቸዋል። አለማየሁ ምንም የደረሰበት ነገር እንደሌለ አሁንም በድጋሚ እናረጋግጣለን ብለዋል።